የአብሮነት ኢትዮጵያ

## ጦርነት ይቁም! ግፋዊ አገዛዝ ያብቃ! ሰላም ይምጣ!!

## የ100 ሺዎች የተቃውሞ ትዕይንተ-ህዝብ ጥሪ በታላቅ የበይነ-መረብ አደባባይ!

### ከ የአብሮነት-ኢትዮጵያ የተሰጠ መግለጫ

በአሁኑ ወቅት ሀገራችን ኢትዮጵያ የምትገኘው ህልውናዋን በሚፈታተን ከፍተኛና ህዝብ ጨራሽ የእርስ-በርስ ጦርነት ውስጥ ነው። በስልጣን ላይ የሚገኘው የብልፅግና አገዛዝ አምባገነናዊና ጦረኛ ከሆነው ባህሪው በመነጨ የአንድ መንግስት ቀዳሚ ተግባር መሆን የሚገባውን ሰላምን እና የህግ የበላይነትን የማስፈን ኃላፊነት መወጣት አልቻለም። ባለመቻሉም የህዝቡን እና የሀገሪቱን ህልውና ከፍተኛ አደጋ ላይ ጥሎታል።

በሌላ በኩል፣ ከአገዛዙ በተፃራሪ የቆሙት ተቀዋሚ ኃይሎች አገዛዙን በብቃት ታግለው ለውጥ በማምጣት ህዝቡንና ሀገሪቱን ከህልውና አደጋ ለመታደግ በሚያስችላቸው የትብብርና የጥንካሬ ደረጃ ላይ አይደሉም። ይህ የሁለት ወገን ድክመት መፍትሄ ካላገኘና በተለይም ተቃዋሚ ኃይሎች ብሄር እና ርዕዮተ-ዓለም ተሻጋሪ የሆነ የጋራ ትብብር ፈጥረው አገዛዙን ታግለው ማሸነፍ ወይም ወደ ሀቀኛ ድርድር እንዲመጣ ማስገደድ ካልቻሉ በስተቀር ሀገሪቱ አሁን ላይ ከገጠማት የህልውና አደጋ የመዳን ዕድሏ እጅግ ጠባብ ይሆናል።

ከዚህ መሰረታዊ ግንዛቤ በመነሳት የወቅቱን የብልፅግና አገዛዝ የጦረኝነት አካሄድና በንጹሀን ላይ እየደረሰ ያለውን ጭፍጨፋ የሚቃዎምና በዓይነቱ የተለየ ታላቅ የተቃውሞ ትዕይንተ-ህዝብ “ጦርነት ይቁም! ግፋዊ አገዛዝ ያብቃ! ሰላም ይምጣ!!” በሚል መሪ ቃል በበይነ-መረብ አደባባይ ለማካሄድ እየተዘጋጀን ነው።

ይህንን ዝግጅት እያካሄደ ያለው የአብሮነት-ኢትዮጵያ ከርዕዮት ሚዲያ ጋር በመተባበር ሲሆን፡ ትዕይንተ-ህዝቡ የሚካሄደውም ቅዳሜ ግንቦት 30 (June 7) ቀን 2017 ዓ.ም ከቀኑ 11 ሰዓት (በዋሽንግተን 10AM፣ በለንደን 3PM) ጀምሮ ይሆናል። ትዕይንተ-ህዝቡ በርዕዮት ሚዲያና በሌሎች የአጀንዳው የጋራ ባለቤትና ተባባሪ የመሆን ፍላጎት ባላቸው በርካታ መገናኛ ብዙሀን በመላው ዓለም ለሚገኘው ኢትዮጵያዊ በቀጥታ ስርጭት ይተላለፋል።

በዚህ ኢትዮጵያውያን የብሄር፣ የኃይማኖትና የርዕዮተ-ዓለም ልዩነት ሳያግዳቸው በጋራ በሚታደሙበት የበይነ-መረብ የተቃውሞ ትዕይንተ-ህዝብ ላይ በወቅቱ የተቃውሞ ትግል የመሪነት ወይም የጐላ የተሳትፎ ሚና ያላቸውና የተለያዩ የፖለቲካ አመለካከቶችንና ማህበረሰቦችን የሚዎክሉ 15 ተዋቂ ሰዎች ተገኝተው ለህዝቡ የቀጥታ ንግግር ያደርጋሉ።

ንግግር እንዲያደርጉ የሚጋበዙት ተዋቂ ሰዎችም የሀገሪቱን የወደፊት ዕጣ-ፈንታ በመወሰን እረገድ የጐላ ሚና የሚኖራቸውና በአሁኑ ወቅት በሰላማዊ ወይም በትጥቅ ትግል ተሳትፎ ያላቸው ሰዎች ይሆናሉ። ንግግር የሚያደርጉበት ርዕሰ ጉዳይም “በሀገራችን ጦርነት ሊቆም፣ አገዛዝነት ሊያበቃና ዘላቂ ሰላም ሊመጣ እንዴት ይችላል?” በሚለው ወቅታዊ ጥያቄ ዙሪያ ይሆናል። በዚህ ትዕይንተ-ህዝብ ተቃውሞ የሚቀርብበት አገዛዝም ፈቃደኛነቱና ድፍረቱ ካለው በትዕይንተ-ህዝቡ ላይ ተገኝቶ አቋሙን እንዲገልፅ ይጋበዛል።

የዚህ ታላቅ ትዕይንተ-ህዝብ መሰረታዊ ዓላማ-

1. በአሁኑ ወቅት የኢትዮጵያ ህዝብ የብልፅግና አገዛዝን የጦረኝነት አካሄድ ምን ያህል አምርሮ እንደሚቃዎምና ዘላቂ ሰላም እንዲመጣ እንደሚፈልግ በተግባር ለማሳየት፣

2. የብልፅግና አገዛዝ የህዝቡን ሰላማዊ የተቃውሞ እንቅስቃሴ በተለመደ የአፈና ድርጊት አዳፍኖ ሊያስቀረው እንደማይችል በተግባር ለማሳየት፣

3. ተቃዋሚ ኃይሎች በልዩነቶቻቸው ላይ ከማተኰር ይልቅ ብሄር-ተሻጋሪ የሆነ ትብብር ፈጥረው ህዝቡን በጋራና በብቃት አታግለው ለአሸናፊነት መብቃት የሚችሉበት ዕድል መኖሩን ለማሳየት፣

4. በሀገራችን የሚዲያ የቀጥታ ስርጭት ታሪክ ለመጀመሪያ ጊዜ ትዕይንተ-ህዝቡን በ100ሺዎች የሚቆጠሩ ኢትዮጵያውያን በአንድ ጊዜና በቀጥታ እንዲታደሙ በማድረግ አዲስና ተከታታይነት ያለው “አገዛዝ-አንቀጥቅጥ” የሆነ የሰላማዊ ትግል ተነሳሽነት በህዝቡ ውስጥ ለመፍጠር ነው።

ስለሆነም የዚህን በዓይነቱ አዲስና ልዩ የሆነ የትግል ስልት ጠቀሜታ በመገንዘብ በሀገር ውስጥና በመላው ዓለም የሚገኘው ኢትዮጵያዊ የትዕይንተ-ህዝቡን የቀጥታ ስርጭት በዬ አለበት ቦታ ሆኖ በመሳተፍ በአገዛዙ የጦረኝነት አካሄድ ላይ ያለውን ተቃውሞ በግልፅ እንዲያሳይ በታላቅ አክብሮት ተጋብዟል።

ከፍ ሲል ለመግለፅ እንደተሞከረው የዚህ ትዕይንተ-ህዝብ ዋና ዓላማ በአሁኑ ወቅት ህዝቡ ምን ያህል የአገዛዙን የጦረኝነት አካሄድ አምርሮ እንደሚቃወምና ከምንም ነገር በላይ ሰላምን ቀዳሚ አጀንዳው አድርጐ እየጠየቀ መሆኑን በተግባር ማሳየት ነው። ስለሆነም አማራጩ ካልጠፋ በስተቀር በተቻለ መጠን ሁሉም ህዝብ በትዕይንተ-ህዝቡ እንዲሳተፍ የሚፈለገው በዩ-ቱዩብ /YouTube/ ወይም የረምብል /Rumble/ የቀጥታ ስርጭት ላይ ነው። ይህም አስፈላጊ የሆነበት ምክኒያት የህዝቡ የተቃውሞ ድምፅ ከፍተኛ መሆኑን ባልተበታተነ ሁኔታ በተጨባጭ የቁጥር መጠን ማሳየት አስፈላጊ ስለሆነ ነው።

የዚህን ታላቅ ትዕይንተ-ህዝብ ፋይዳ ከፍተኛነት በመገንዘብ ህዝቡ በእለቱ እራሱን ከሌሎች ተግባራት ነፃ አድርጐና የኢንተር-ኔት አገልግሎት የሚያገኝበትን ሁኔታ አስቀድሞ በማመቻቸት የትዕይንተ-ህዝቡ ቀጥተኛ ተሳታፊ ሊሆን ይገባል እንላለን። ይህ ትዕይንተ-ህዝብ ውጤታማ ይሆን ዘንድም ሁሉም የህብረተሰብ ክፍል በተለይም የፖለቲካ ድርጅቶች፣ መገናኛ ብዙሀንና ማህበራዊ አንቂዎች ህዝቡን በስፋት በመቀስቀስ ረገድ ኃላፊነታችሁን እንድትወጡ በአክብሮት እንጠይቃለን።

ከሁሉም በላይ መገናኛ-ብዙሀን ትዕይንተ-ህዝቡን በዩ-ቱዩብ ወይም በራምብል በቀጥታ በማሰራጨትና አድማጮቻችሁ በከፍተኛ መጠን የቀጥታ ስርጭቱን እንዲከታተሉ አስቀድማችሁ በስፋት በመቀስቀስ የዚህ ታላቅ ዝግጅት የጋራ ባለቤትና ተባባሪ ልትሆኑ ይገባል እንላለን። በትዕይንተ-ህዝቡ ላይ ንግግር እንድታደርጉ የምትጋበዙ ተዋቂ የፖለቲካ ሰዎችም የአጀንዳውን ታላቅነትና ወቅታዊነት በመገንዘብና ለምናቀርብላችሁ ግብዣ ቀዳሚ ትኩረት በመስጠት ለዘላቂ ሰላም መምጣት ያላችሁን ቁርጠኛነት በተግባር እንደምታሳዩ ተስፋ እናደርጋለን።

የዚህ ትዕይንተ-ህዝብ ሂደት እግረ-መንገዱንም በሀገሪቱ የፖለቲካ ሂደት በተለያዩ መንገድ ተሳትፎ ካላቸው የፖለቲካ ኃይሎችና መገናኛ-ብዙሀን መካከል ህዝቡ የዘላቂ ሰላም ባለቤት እንዲሆን የትኞቹ አካላት ልባዊና ቁርጠኛ አቋም እንዳላቸው ጥሩ የማሳያ አጋጣሚ ይሆናል ብለንም እናምናለን።

በመጨረሻም፣ ለዚህ ታላቅ ዝግጅት ስኬታማነት የተለያዩ ትብብር ለማድረግ የምትፈልጉ አካላት በዚህ መግለጫ ግርጌ ላይ በተቀመጠው የኢ-ሜይል አድራሻችን ልታገኙን እንደምትችሉ በዚህ አጋጣሚ በአክብሮት እንገልፃለን።

## ስንተባበር እናሸንፋለን!!

የአብሮነት-ኢትዮጵያ

ግንቦት 11 ቀን 2017 ዓ.ም.

Email: ye.abronet2016@gmail.com